# በፍትሐብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ (፫) ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ጥቂት ፡ አስተያየቶች ።

## በከሳሽ ፡ ገብረማርያም ፡ አመንቴና ፡ ተከሳሽ ፡ቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ላይ ፡ የቀረበ ፡ አስተያየት ፡

በብረን—ኦቶ ፡ ብሪዴ* ፡ የተጻፈ ።

ዋስትና ፡- አንድ ፡ ሰው ፡ (ዋሱ) ፡ ለባለ ፡ ገንዘቡ ፡ የባለዕዳውን ፡ ግዴታ ፡ አስ ፈጽማለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚገባው ፡ ውል ፡ (የፍ. አን. ፩ሺ፱፻፳) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ግዴታን ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የሆነ ፡ የተለመደ ፡ ዘዴ ፡ ነው ። ስለዚህም ፤ ከአን. ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ እስከ ፡ አን. ፩ሺ፱፻፵፩ ፡ ያሉት ፡ የፍትሐብሔር ፡ አንቀጾች ፡ መብራራት ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚችል ፡ አስፈላጊ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ባለፈው ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ከፈጠሩት ፡ አንደኛው ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ (፫) ፡ ነው ። በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ዋስትና ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ እንዲኖረው ፡ ከተፈለገ ፡ ዋሱ ፡ አስመልሳለሁ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ የሚገባበት ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ መጠን ፡ በዋስትናው ፡ ውል ፡ ጽሑፍ ፡[1] መስፈር ፡ አለበት ።[2] በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ምክንያት ፡ የሚያጋጥሙን ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ችግሮች ፡ ዓንቀጹ ፡ አሻሚ ፡ ሆኖ ፡ ትርጉም ፡ ስላሻው ፡ ሳይሆን ፤ አንቀጹ ፡ የሚያዘው ፡ ከኖረው ፡ ያገሪትዋ ፡ አሰራር ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ችግሩ ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ያልነበረውን ፡ የዋጋ ፡ መጠን ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲሠፍር ፡ ማድረጉ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ከዚህ ፡ በበለጠ ፡ ደግሞ ፡ ዋስትና ፡ ለሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ጥቅም ፡ ከሚያስገኛቸው ፡ ከዋና ፡ ጠቃሚ ፡ ነገሮች ፡ አንደኛውን ፡ በአደጋ ፡ ላይ ፡ ስለሚጥልም ፡ጭምር ፡ ነው ። እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አሰራር ፡ ከሆነ ፡ አንድ ፡ የዋስትና ፡ ግዴታ ፡ የሚገባ ፡ ሰው ፡ ሥራው ፡ ዋስ ፡ በመሆን ፡ አንድ ፡ እዳን ፡ ማስመለስ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ተያዥ ፡ በመሆን ፡ ደግሞ ፡ ያንድ ፡ ተቀጣሪን ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።[3] በሁለተኛው ፡ ሁኔታ ፤ የዋስትናው ፡ ውል ፡ በሚከናወንበት ፡ ጊዜ ፡ ተያዡ ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችለው ፡ ጉዳት ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ። ስለዚህም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ የዋስትና ውለታ ፡ ላይ ፡ የአንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ (፫) ፡ ጥቅም ፡ ጨርሶ ፡ ዋጋ ፡ ባያጣም ፡ እንኳ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ።[4] ያንድን ፡ ተቀጣሪን ፡ መልካም ፡ ተግባር ፡ ማረጋገጫ ፡ ሆኖ ፡ በሰፊው ፡ እስራ ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ የቆየውን ፡ ዋስትናን ፡ ስንመለከት ፡ ይህን ፡ ያዲሱ ፡ ፍትሐብሔር ፡ ውጤት ፡ ላለመደገፍ ፡ የሚደረገው ፡ ሙከራ ፡ እጅግም ፡ ሊያስገርመን ፡ አይችልም ።

አንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ (፫) ፡ የሚለው ፡ ለተያዥ ፡ ውል ፡ ተስማሚ ፡ አለመሆኑ ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ የዋስትናን ፡ አንቀጾች ፡ ሲያረቅ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባሕል ፡ ውስጥ ፡

---

* የጁሪስ ፡ ፕሩዳንስ ፡ ዶክተር ፡ (ሀምበርግ) ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፤ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ።

1. የዋስትና ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፲፯፻፳፭) ፡ እንዲሁም ፡ በሁለት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ መፈጸም ፡ አለበት ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፯፻፳፯) ።
2. ለግዴታው ፡ ዋስ ፡ የሆነበት ፡ የገንዘቡ ፡ ልክ ፡ በዋስትና ፡ ውል ፡ ካልተገለጸ ፡ ዋስትናው ፡ ፈራሽ ፡ ነው ።
3. በቅርቡ ፡ አንድ ፡ የራዲዮ ፡ ቴክኒሽያን ፡ ሆኖ ፡ ለመቀጠር ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ እንደተጠየቀው ፡ ሁሉ ፤ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ጋዜጦች ፡ የሚወጡ ፡ የሥራ ፡ ማስታወቂያዎች ፡ የተያዥ ፡ አስፈላጊነትን ፡ እንደሚገልጹ ፡ ለመረዳት ፡ አያዳግትም ።
4. እንደዚሁ ፡ ያሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ለመንግሥት ፡ የሚያስከትሉት ፡ ችግር ፡ አስቀያስ ፡ አሰፋ ፡ በጻፈው ፡ የሪሰርች ፡ ጽሑፍ ፡ በዝርዝር ፡ ተነግሯል ፤ "Guarantee for Fidelity of Employees in the Government Machinery of Ethiopia," (አልታተመም ፤ አርካይቭ ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ።)

ብኖረው ፡ በዋስትና ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ እንዲሠሩ ፡ ነው ፤ የሚለውን ፡ አስተያየት ፡ አስከትለዋል ። ይህን ፡ በሚሉ ፡ ሰዎች ፡ አስተያየት ፡ በተያዥ ፡ ውል ፡ ላይ ፡ የሚሰሩት ፡ የባሕላዊ ፡ ሕጎች ፡ ናቸው ። የአዲስ ፡ አበባው ፡ ከፍተኛ ፡ ፍ/ቤትም ፡ ይኸንኑ ፡ አስተሳሰብ ፡ ይከተላል ። ስለዚህም ፤ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የተባለው ፡ ከፍተኛ ፡ የዋጋ ፡ መጠን ፡ ባይገለጽም ፤ ተያዥ ፡ ታማኝ ፡ ያልሆነው ፡ ተቀባሪ ፡ ለሚያደርሰው ፡ ጉዳት ፡ መክፈል ፡ አለበት ፡ ሲል ፡ የፈረደውን ፤ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ እንዲሽረው ፡ ተገድደዋል ።[5] በሁለቱም ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሁለቱም ፡ ዓይነት ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ ልዩነት ፡ የማይፈጥረውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ አንጋገር ፡ ለመሸሸግ ፡ እንደማይቻል ፡ ገልጾ ፡ ተናግረዋል ። በሁለተኛው ፡ ውሳኔ ፤[6] ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ውሳኔዎች ፡ የሚደግፉትን ፡ ሐሳቦች ፡ አብራርቶ ፡ የጻፈው ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ አስተያየት ፡ ያጠቃልል ፡ ይሆናል ።

ጠቅላይ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተመሳሳይ ፡ አስተያየቶች ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ የከፍተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ መሻሩ ፡ ብቻ ፡ የምንነጋገርበትን ፡ ችግር ፡ አስደሳች ፡ ከማድረጉም ፡ በላይ ፡ ችግሩን ፡ በበለጠ ፡ ማብራራት ፡ ተገቢ ፡ መሆኑን ፡ ያሳያል ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ አርእስት ፡ "ስለ ፡ ዋስትና ፡ ፎርም" ፡ ነው ። እንዲሁም ፤ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንደሚገለጸው ፤ የአንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፳፪ ፡ (፫) ፡ አስፈላጊነት ፡ የፎርሙን ፡ ጥያቄ ፡ በማሟላት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ እንኳ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንቀጹን ፡ ቻል ፡ ማለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሕጉ ፡ የሚለውን ፡ በቀጥታ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ፈቃደኛ ፡ ላለመሆናቸው ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ። ይህን የፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ አዝማሚያ ፡ የሚያመለክቱ ፡ ምሳሌዎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ከሳሽ ፡[7] አቫኪያን ፡ ተከሳሽ ፡ አቫኪያን ፡ ክስ ፡ ሲሆን ፤ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ ሕጉ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ለአንድ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ከታወጀ ፡ ወዲህ ፡ የጉዲፈቻ ፡ ልጅ ፡ ለሆነ ፡ ውርስ ፡ ይገባዋል ፡[8] ተብሎ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፰፻፶) ፡ እና ፡ የአሥመራው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጠ/ፍርድ ፡ ቤት ፡ በፈረደው ፡ መሠረት ፡ ሕጉ ፡ በሚያዘው ፡ ፎርም ፡[9] ያልሆነውን ፡ አንድ ፡ የመሬት ፡ ሽያጭ ፡ ውል ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ የዋሉት ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ክሶች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ተደናቂ ፡ ናቸው ።

---

5. ከሳሽ ፡ ከተማ ፡ ኃይሌ ፡ ተከሳሽ ፡ የመብራት ፡ ኃይል ፡ ባለሥልጣን ፡ ፮ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ (፲፱፻፷፱) ገጽ ፡ ፴፰ ፡ እና ፡ የሚከተሉት ። ከሳሽ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ አመንቴ ፡ ተከሳሽ ፡ ቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ፰ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ (፲፱፻፷፬) ፡ ገጽ ፡ ፴ እና ፡ የሚከተሉት ፡

6. እላይ ፡ በተራ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ የተጠቀሰው ፤ ከሳሽ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ አመንቴ ፤ ተከሳሽ ፡ ቴሌኮሙኒኬሽን ።

7. ፩ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ (፲፱፻፶፱)ገጽ ፡ ፭፫ ፡ እና ፡ የሚከተሉት ። ይህ ፡ ክስ ፡ በሰፊው ፡ ተጽፎበታል ። እንዲታተምም ፡ ተደርጓል ፤ ለምሳሌ ፡ ቫንደርሊንደን ፤ Introduction au droit de l'Ethiopie moderne (Paris 1971) ፤ ገጽ ፡ እንዲሁም ፡ በዘ_ያው ፡ ጸሐፊ ፡ "Civil Law and Common Law Influences on Developing Law of Ethiopia" 16 *Buffalo L. Rev*, (፲፱፻፷፯) ፤ ገጽ ፡ ፪፻፶ ፡ እና ፡ የሚከተሉት ፡ በገጽ ፡ ፪፻፷፬ ፡ ላይ ፤ እና ፡ "Quelques aspects fondamentaux du development juridique Ethiopien"; *Verfassung and Recht in ubersee*, ቮልዩም ፡ ፫ ፡ (፲፱፻፸) ገጽ ፡ ፪፰፯ ፡ እና ፡ የሚከተሉት ፡ ገጽ ፡ ፪፹፬ ።

8. የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍ/ቤት ፤ ከሳሽ ፡ ጀጀብ ፡ ቢሽ ፡ ተከሳሽ ፡ ሞላ ፡ ደሌ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁ. ፩ሺ፫፻፺፯/፷ ፡ (ያልታተመ) ።

9. የአሥመራው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጠ/ፍርድ ፡ ቤት ፤ ከሳሽ ፡ ብርሃን ፡ ኃይሌ ፤ ተከሳሽ ፡ አሥመሮም ፡ ተድላ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፬፻፷፮ ፡ (ያልታተመ) ።

፩ኛ/ ሕጉ ፡ የሚለውን ፡ አለመከተል ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በተወሰኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ አይደለም ። የበላይና ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ ፍርዳቸው ፡ ተመሳሳይ ፡ አይደለም ። ለምሳሌ ፡ በአቫኪያን ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሕጉን ፡ ትእዛዝ ፡ ሲያከብር ፡[10] የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ ሽሮታል ። ፪ኛ/ ይህ ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ዳኞቹ ፡ በቂ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ስለሌላቸው ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ልክ ፡ አይደለም ። እንዲያውም ፡ ዳኞቹ ፡ አንቀጾቹን ፡ ለይተው ፡ ማወቃቸውና ፡ እንዲሁም ፡ እነዚያው ፡ አንቀጾች ፡ ለምን ፡ እክሶቹ ፡ ላይ ፡ ለመሥራት ፡ እንደማይችሉ ፡ ለማሳየት ፡ የሚያቀርቡት ፡ የሕግ ፡ አስተሳሰብ ፡ የሚያሳየው ፡ የተባለው ፡ ዕውቀት ፡ እንዳልጐደላቸው ፡ ነው ። እንዲያውም ፤ በእነዚህ ፡ ክሶች ፡ የቀረቡት ፡ የሕግ ፡ አስተሳሰቦች ፡ ፍርዳቸው ፡ ትክክል ፡ ከሆኑት ፡ ሌሎች ፡ ክሶች ፡ ይልቅ ፡ በይበልጥ ፡ የተራቀቀ ፡ ነው ።[11]

ስለዚህም ፡ እላይ ፡ ለተጠቀሱት ፡ ፍርዶች ፡ መሠረታዊው ፡ ምክንያት ፡ ሕጉን ፡ በትክክል ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ቢያውሉት ፡ ፍትህ ፡ ይጓደላል ፡ የሚለው ፡ ነው ። ይህንን ፡ የፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ስሜት ፡ የማያስወግዱበት ፡ ምክንያት ፡ ወደው ፡ እንዳልሆነ ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ። የውል ፡ ስጭውንም ፡ ሆነ ፡ የተቀባዩንም ፡ ፍላጐት ፡ በግልጽ ፡ በሚያሳዩበትም ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ቢሆንም ፡ ሕጉ ፡ የሚለውን ፡ በቀጥታ ፡ አልተከተሉም ፡ ብሎ ፡ ኑዛዜንም ፡ ሆነ ፡ ውሎቹን ፡ ማፍረስ ፡ ሳልተማረው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሕግ ፡ ትምህርትም ፡ ላላቸው ፡ ቢሆን ፡ መቀበሉ ፡ አዳጋች ፡ ነው ። ይህ ፡ ችግር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ በአፍሪካ ፡ እንዲያውም ፡ በሚያድጉ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ አይደለም ። በሌሎቹም ፡ ሀገሮች ፡ ቢሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አንድን ፡ ሕግ ፡ በቀጥታ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋሉ ፡ አንድ ፡ ጥብቅና ፡ ያልተፈለገ ፡ ውጤት ፡ የሚያስከትል ፡ ሲሆን፤ በእንደዚህ ፡ ባለው ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ሕጉን ፡ አይጠቀሙበትም ።[12] ሆኖም ፤ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ችግሩን ፡ የሚያባብሱ ፡ ብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሕጎቹ፡ አዲስ ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ ሕጎቹ ፡ የሚሉት ፡ ገና ፡ በሕዝቡ ፡ አይታወቁም ፡ እንዲሁም ፡ የጠበቃን ፡ እርዳታ ፡ ማግኘት ፡ ገና ፡ አልተለመደም ። የአንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፷፪ ፡ (፫) ፡ ጥያቄም ፡ የሚያሳየው ፡ ሕጎቹን ፡ አለማወቅ ፡ ባልተማሩት ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ አይደለም ። ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውድቅ ፡ ያደረጋቸው ፡ ሁለቱም ፡ የዋስትና ፡ ውሎች ፡ ውድቅነታቸው ፡ የተወሰነው ፡ በሕዝባዊ ፡ ባለሥልጣን ፡ ነው ። እንደገናም ፡ ከታላላቅ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ባንኮች ፡ አንደኛው ፡ ከአንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፷፪ ፡ (፫) ፡[13] ጋር ፡ ለማይስማሙ ፡ ሕጐች ፡ የውል ፡ ፎርም ፡ ይጠቀማል ። ስለዚህም ፡ በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ ሕጉን ፡ ያለማወቅ ፡ ለይቅርታ ፡ ምክንያት ፡ ባይሆንም ፡ እንኳ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሁኔታ ፡ ችግሩን ፡ ሊመረዳት ፡ ይቻላል ። ይኸም ፡ ሁኔታ ፡ ተቸግረው ፡ ወደ ፡ እነሱ ፡ የሚሄዱትን ፡ ሰዎች ፡ ሕጉ ፡ በሚያዘው ፡ ፎርም ፡ እንዳይተዳደሩ ፡ በማድረግ ፡ ለመርዳት ፡ ዳኞች ፡ ይፈተኑ ፡ ይሆናል ።

10. እላይ ፡ በ፯ኛ ፡ ተራ ፡ ቁጥር ፡ የተመለከተውን ፡ አገናዝብ ።

11. ይህ ፤ ጠ/ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በከሳሽ ፡ አቫኪያን ፡ ተከሳሽ ፡ አቫኪያን ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ በሰጠው ፡ ፍርድና ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ቤት ፡ ደግሞ ፡ በተያዥ ፡ ክሶች ፡ ላይ ፡ ያደረጋቸው ፡ ውሳኔዎች ፡ እንዲያውም ፡ በተለይ ፡ ይነፃፀራሉ ።

12. በጀርመን ፡ አሠራር ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፤ የጀርመን ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፫፻፲፫ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ሽያጭ ፡ ውል ፡ ዋጋ ፡ እንዲኖረው ፡ ከተፈለገ ፡ በኖታሪ ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ሲል ፡ የሚያዘው ፡ በከፊል ፡ እየቀረ ፡ ሄዷል ። ይኸም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ከፍትሕ ፡ ጋር ፡ አሠራሩ ፡ የማይስማማ ቢሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ አንቀጹን ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ፈቃደኞች ፡ ስላልሆኑ ፡ ነው ።

13. ለብድር ፡ ተያዥ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ብድሩን ፡ ሳይከፍል ፡ ቀርቶ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ወለድም ፡ መክፈል ፡ አለበት ። ስለዚህ ፡ የዚህ ፡ ግዴታ ፡ ከፍተኛው ፡ መጠን ፡ አይጸናም ።

ይህ ፡ የቀረበው ፡ ሃሳብ ፡ በሌሎችም ፡ አስተያየቶች ፡ ሊደገፍ ፡ ይቻላል ። በአንድ ፡ ተሚልቶ ፡ በደረጃ ፡ የሕግ ፡ ሲስተም ፡ ውስጥ ፤ ከፍ ፡ ባለ ፡ ሁኔታ ፡ የሠለጠነው ፡ ፕሮ ፌሽናላዊው ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ክፍል ፡ የራሱ ፡ የሆነ ፡ አስተያየትና ፡ የፍትህ ፡ አተ ረጓጐም ፡ አለው ። እነዚህ ፡ አስተያየቶች ፡ ሁልጊዜ ፡ ካልተማረው ፡ ሰው ፡ አስተ ያየቶች ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ አይደሉም ። የሕግ ፡ ዐዋቂው ፡ አስተያየት ፡ እንደ ፡ የሕግ ፡ እርግጠኛነትንና ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ መፋጠን ፡ እንዲሁም ፡ መከናወን ፡ ይጨምራል ። እነዚህ ፡ አስተያየቶች ፡ ደግሞ ፡ ከመግለጻቸው ፡ በፊት ፡ በፍትህ ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ ለማይገኙ ፡ ሰዎች ፡ ግልጽ ፡ አይደሉም ። አንድ ፡ የሕግ ፡ አዋቂ ፡ በፎርሙ ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ የተወሰነን ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ በሌሉበት ፡ የተሠጠን ፡ ፍርድ ፡[14] ትክክል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ እያስቸ ግረውም ። ያልተማረው ፡ ሰው ፡ ግን ፡ በእንደነዚህ ፡ ዓይነቶቹ ፡ ውሳኔዎች ፡ ይከፋ ፡ ይሆናል ። ሆኖም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍትህ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎችና ፡ የሕዝቡ ፡ አስተያየት ፡ ልዩነት ፡ ገና ፡ ስላልጐላ ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎቹ ፡ ስለፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ዎች ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፡ ከሕዝቡ ፡ አስተያየት ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፤ አንድ ፡ ተያዥ ፡ በቃሉ ፡ መሠረት ፡ ኃላፊነቱን ፡ መቀበል ፡ አለበት ፡ እንጂ ፡ ኃላፊነቱን ፡ በአንድ ፡ ባልታወቀ ፡ የሕግ ፡ ትዕዛዝ ፡ ምክንያት ፡ ማስወገድ ፡ የለበትም ፡ ብለው ፡ ያስባሉ ።

ይህ ፡ ትክክል ፡ ከሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ሕጉ ፡ የሚለውን ፡ አልተከተላችሁም ፡ ብሎ ፡ መውቀስ ፡ በቂ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ውሳኔያቸው ፡ እንዳይሻር ፡ ወይም ፡ በመጽሔቶች ፡ በሚሠፍሩ ፡ የዐዋቂዎች ፡ ጽሑፍ ፡ እንዳይወቀሱ ፡ በማሰብ ፡ ወደፊት ፡ በዚያው ፡ ቢቀጥሉም ፡ እንኳ ፡ ጽሑፋቸው ፡ የጠለቀ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። ማድረግ ፡ የሚገባቸው ፡ የተባሉት ፡ አንቀጾች ፡ የወጡበትን ፡ ምክንያት ፡ መግለጽ ፡ ነው ። ሌላ ፡ ዓላማ ፡ ሳይኖረው ፡ ሕጋዊ ፡ ዝምድና ፡ ለመፍጠር ፡ የወጣም ፡ ሕግ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ በዚሁም ፡ ሳቢያ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ የሚያፋጥን ፡ ቢሆን ፤ እነዚሁ ፡ እራሳቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ዓላማዎች ፡ ስለሆኑ ፡ ተደጋፊ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ስንመለከት ፡ ጥቅም ፡ የሌላቸው ፡ የሚመስሉ ፡ ብዙዎች ፡ ሕጐች ፡ አተኩረን ፡ ስንመለከታቸው ፡ መብትንና ፡ ግዴታን ፡ የሚሠጡ ፡ ሆነው ፡ እናገኛቸዋለን ። ማለትም ፤ የሚመለከቱት ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለተዋዋዮቹም ፡ ፍትህን ፡ ያስገኛሉ ። ለዚህም ፡ ምሳሌ ፡ ከሚሆኑት ፡ አንደኛው ፡ የሚሠጡት ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ነው ። አንድ ፡ ግዴ ታን ፡ የሚቀበል ፡ ሰው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ መግባቱን ፡ መገንዘብ ፡ አለበት ፤ እንዲሁም ፡ በኑሮ ፡ ውስጥ ፡ እንደምናየው ፡ ከሆነ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በምስክሮች ፡ መካከል ፡ ከመፈራረም ፡ ይልቅ ፡ በቃል ፡ ተስፋ ፡ መስጠቱ ፡ ይቀላል ። ለኢኮኖሚ ፡ ዋና ፡ የሆነ ውን ፡[15] የመሬትን ፡ ሽያጭና ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሚቆዩትን ፡ ውሎች ፡[16] የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የሚያዘው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

በዋስትናም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ የሕጐች ፡ ማስጠንቀቅ ፡ ሥራ ፡ የተለየ ፡ አስ ፈላጊነት ፡ አለው ።[17] የዋስትና ፡ ውል ፡ ደካማነት ፡ አንድን ፡ ሰው ፡ ለሌላ ፡ ኃላፊ ፡

---

14. ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ ፍ/ቤት ፡ በማይቀርቡበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ፍ/ቤቶቹ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ አንቀጾች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማያውሉበት ፡ ጉዳይ ፤ ዳንኤል ፡ ገብሬ ፡ ኪዳነን ፡ ተመልከት ፡ "Causes of Delay in Court," ፲፱፻፷፩ ፡ (ያልታተመ) ፤ አርካይቭ ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ) ፤ ገጽ ፡ ፳—፵፩ ፤ እና ፡ ገሰብ ፡ ዳፍላ ፤ "Causes and mechanisms of Delay in Courts" ፲፱፻፷፩ ፡ (ያልታተመ ፤ አርካይቭ ፤ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፤ ቀ. ኃ. ሥ. ዩኒቨርሲቲ) ፤ ገጽ ፡ ፩—፳ ።
15. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፰፻፸፯ ፡ እና ፡ እንዲሁም ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፯፻፳፫ ።
16. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፯፻፳፭ ።
17. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፯፻፳፭(ሀ)ን ፡ ተመልከት ።

ማድረጉ ፡ ነው ። የዋሱ ፡ ኃላፊነት ፡ የሚወሰነው ፡ ከእሱ ፡ ከራሱ ፡ ቁጥጥር ፡ ውጭ ፡ የሆነው ፡ ዋስትናውን ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ ኃላፊነቱን ፡ እንደአወረደ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ዋሱ ፡ በግድ ፡ የለሽነት ፡ እንደዚህ ፡ ካለው ፡ ውል ፡ እንዳይገባ ፡ በማሰብ ፡ ውሉ ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲሆን ፡ ሕጉ ፡ ያዛል ። ሆኖም ፡ ይህ ፡ ለዋሱ ፡ ተብሎ ፡ የተደረገው ፡ ነገር ፡ በቂ ፡ መሆኑ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ለአምስት ፡ ብር ፡ ዋስትና ፡ የሰጠ ፡ ሰው ፡ ከዚያ ፡ የገንዘብ ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ ውሉ ፡ ያመጣብኛል ፡ ብሎ ፡ አያስብም ። ግን ፡ ይህ ፡ አስተያየት ፡ ሁልጊዜ ፡ ትክክል ፡ ላይሆን ፡ ይችላል ። የዋሱ ፡ ግዴታ ፡ ከባለዕዳው ፡ ግዴታ ፡ ጋር ፡ ያለውሳኔ ፡ የሚመሳሰል ፡ ከሆነ ፡ አምስት ፡ ብሩ ፡ በካሣ ፡ ወለድ ፡ ምክንያት ፡ በዝቶ ፡ ዋስትና ፡ ሰጭው ፡ በመጀመሪያ ፡ ካሰበው ፡ በላይ ፡ ሊከፍል ፡ ይችላል ። ስለዚህ ፡ ዋሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ለማይታየውና ፡ ከእሱ ፡ ቁጥጥር ፡ ውጭ ፡ በሆነው ፡ ጉዳይ ፡ እጁን ፡ ይጨምራል ፡ ማለት ፡ ነው ።

አንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፷፪ ፡ (፫) ፡ የግዴታውን ፡ ከፍተኛ ፡ የገንዘብ ፡ መጠን ፡ መወሰን ፡ አለበት ፡ የሚለው ፡ እነዚህን ፡ ችግሮች ፡ ለማስወገድ ፡ በማሰብ ፡ ነው ። ማለትም ፡ ሕጉ ፡ ዋሱ ፡ የሚገባበትን ፡ ዕዳ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲረዳው ፡ በማለት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ በማድረጉ ፡ ሕጉ ፡ በዋስትና ፡ በኩል ፡ ፍትሐብሔሩ ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ ያልነበረውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓታዊ ፡ አቋም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሚመሠርተው ፡ እንዲሁም ፡ ያለገደብ ፡ ሰዎች ፡ ሲፈጸጸሙት ፡ የነበረውን ፡ የዋስትና ፡ አስተሳሰብን ፡ በጣም ፡ ይለውጠዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ የተደረገው ፡ በአጥጋቢ ፡ ምክንያቶች ፡ ነው ። የአንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፷፪ ፡ (፫) ፡ መመሪያ ፡ ይህ ፡ ሲሆን ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንቀጹ ፡ ለአንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ዕዳ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለተያዥ ፡ አይሠራም ፡ ሲል ፡ የሚጥሰው ፡ የሕጉን ፡ አነጋገር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አንቀጹ ፡ እራሱ ፡ የተመሠረተበትን ፡ አስተሳሰብም ፡ ነው ። እንዲያው ፡ ተያዡን ፡ አስቀድሞ ፡ ሊያየው ፡ በማይችለው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ እጁን ፡ እንዳያገባ ፡ መከላከሉ ፡ በበለጠ ፡ አስፈላጊና ፡ ግልጽም ፡ ነው ።

የአንድ ፡ የተለመደ ፡ ዓይነት ፡ ዕዳ ፡ መጠን ፡ (ለምሳሌ ፡ ከሽያጭ ፡ ውል ፡ ለሚገኝ ፡ ግዴታ ፡ እንደሚሆን ፡ መብት) ፡ ከወለዱ ፡ ወይም ፡ ከካሳው ፡ መጠን ፡ የሚልቀው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ዋሱ ፡ ለሚገባበት ፡ ግዴታ ፡ ልክ ፡ ይህን ፡ መጠን ፡ እንደመመሪያ ፡ አድርጎ ፡ ሊወስደው ፡ ይችላል ። በአንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በአቀጣጠር ፡ ውል ፡ ጊዜ ፡ ተቀጣሪው ፡ በቀጣሪው ፡ ላይ ፡ የሚያመጣውን ፡ ጉዳት ፡ አስቀድሞ ፡ ለመገመት ፡ አይችልም ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ጉዳቱ ፡ ተቀጣሪው ፡ በተከለከለው ፡ ቦታ ፡ ሲጃራ ፡ ሲያጨስ ፡ የካምፓኒውን ፡ ቤት ፡ ያቃጥል ፡ ይሆናል ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ጉዳት ፡ ገንዘብን ፡ የሚያመለክት ፡ አይደለም ።

ስለዚህም ፡ ያለአንቀጽ ፡ ፩ሺ፱፻፷፪ ፡ (፫) ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ ተያዥ ፡ መሆን ፡ በጣም ፡ አደገኛ ፡ ሥራ ፡ ነው ። ሰዎች ፡ ይህን ፡ አደጋ ፡ ሳይገነዘቡ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተያዥ ፡ እንሆናለን ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ይሰጣሉ ። ይኸን ፡ ከሚያስደርጓቸው ፡ ነገሮች ፡ እንደኛው ፡ ለአንድ ፡ ሥራ ፡ ለአገኘ ፡ ዘመድ ፡ ወይም ፡ ወዳጅ ፡ እምቢ ፡ ማለቱ ፡ በሕብረተሰቡ ፡ ዘንድ ፡ የሚያስከፉ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

እንዲህ ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ ሕጉ ፡ ዋሱንም ፡ ሆነ ፡ ተያዡን ፡ የሚገባበትን ፡ ዕዳ ፡ መጠን ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲረዳው ፡ የሚያደርገውን ፡ የዕዳው ፡ ብዛት ፡ እንዲጻፍ ፡ ማዘዙ ፡ ትክክለኛ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ስለዚህም ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በከሳሽ ፡ ገ/ማርያም ፡ አመንቴ ፡ ተከሳሽ ፡ ቴሌኮሙኒኬሽን ፡[18] ክስ ፡ ውስጥ ፡ ይኸንኑ ፡ አስተያየት ፡ ስለደገፈ ፡ ተቀባይነት ፡ አለው ።

18. እላይ ፡ በ፩ተኛው ፡ ተራ ፡ ቁጥር ፡ የተጠቀሰውን ፡ ተመልከት ።

ተያዥነት ፡ አንድ ፡ ታማኝ ፡ ካልሆነ ፡ ተቀጣሪ ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ለማድረግ ፡ በማያስችል ፡ ሁኔታ ፡ የተሰጡት ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየቶች ፡ በዚህ ፡ ዘዴ ፡ ካልታመኑ ፡ ተቀጣሪዎች ፡ እራሳቸውን ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚፈልጉ ፡ ቀጣሪዎች ፡ ይከፋበት ፡ ይሆናል ። ሆኖም ፡ የታማኝነት ፡ ኢንሹራንስ ፡ (fidelity insurance)[19] ለሠራተኞቻቸው ፡ በማውጣት ፡ እራሳቸውን ፡ ሊጠብቁ ፡ ይችላሉ ። እንዲያውም ፡ ከመጀመሪያው ፡ ይልቅ ፡ የተሻለ ፡ ዘዴ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ የተያዡንም ፡ ሆነ ፡ የተቀጣሪውንም ፡ እንዲሁም፡ የቀጣሪውን ፡ ፍላጐት ፡ ያሟላል ። ቀጣሪው ፡ እንደተቀጣሪው፡ ታማኝ ፡ ላይሆን ፡ ከሚችለው ፡ ከተያዡ ፡ ገንዘቡን ፡ ከሚያገኝ ፡ ይልቅ ፡ ከኢንሹራንሱ ፡ ማግኘት ፡ በበለጠ ፡ የተረጋገጠ ፡ ይሆንለታል ። ዘመድ ፡ የሌለውም ፡ ሥራ ፡ ፈላጊ ፡ ተያዥ ፡ ሳያመጣ ፡ ለመቀጠር ፡ ይችላል ። ዕዳም ፡ ቢመጣ ፡ ሥራዬ ፡ ብለው ፡ የያዙት ፡ የኢንሹራንስ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ይከፍላሉ ፡ እንጂ ፡ ተያዥነት ፡ የሚያስከትለውን ፡ ዕዳ ፡ አስቀድሞ ፡ ለመረዳት ፡ የማይችለው ፡ ገና ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይለኛል ፡ ብሎ ፡ ተያዥ ፡ የሚሆነው ፡ ሰው ፡ አይከፍልም ፡ ማለት ፡ ነው ።

19. ይሄው ፡ መፍትሔ ፡ ይሻላል ፡ ብሎ ፡ እስቅያስ ፡ አሰፋም ፡ ይስማማል ፤ እላይ ፡ በ፩ኛው ፡ ተራ ፡ ቁጥር ፡ ተጠቅሶአል ።